# ታሪካዊ ስህተት ከማሰራት ተጠበቁ

*ኢብሳ ነሜ 1/23/13*

ከጥቅምት ወር ወዲህ ዘንድሮ የሚካሄደውን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደር እንዲሁም የአካባቢ ም/ቤቶች አባላት ምርጫ ጋር የታይዞ የጋዜጦች የፊት ገፅ ላይ የተለመደው "33ቱ ፓርቲዎች" የሚል የዜና ርዕስ ባለፈው ሳምንት ወደ ሃያ ስምንት (28) ተቀይሯል፡፡ በሌላ በኩል ምርጫው ላይ ለመሳተፍ የተመዘገቡ ፓርቲዎች 29 መድረሳቸው ተዘግቧል፡፡ ከፓርቲዎቹ ማሃከል ይበጀኛል የሚሉዋን የሚመርጠዉም ሕዝብ እንዲሁ እየተመዘገበ ነው፡፡

የዚህ ፅሁፍ ዋና ትኩረት ቀደም ሲል "33ቱ" ይባሉ የነበሩት አሁን ቁጥራቸው ወደ 28 ዝቅ ያለው ፓርቲዎች የያዙት አቋም ላይ ነው፡፡ እንደምናስታወሰው ፓርቲዎቹ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ ለመወያየት የጠራው ስብሰባ ላይ፣ ከምርጫው በፊት ምላሽ ማግኘት አለባቸው ያሉዋቸውን 18 ጥያቄዎች አንስትው ነበር ምርጫው ላይ ያለመሳተፍ አዝማሚያ ማሳየት የጀመሩት፡፡ ይህን ተከትሎ የምርጫ ቦርድ ላቀረበዋቸው ጥያቄዎች በሙሉ አንድ በአንድ ምላሽ ሰጠ፡ ያቀረበዋቸው ጥያቄዎችና ቦርዱ የሰጠው ምላሽ በተደጋጋሚ የተገለጹ ቢሆንም፣ ለማስታወስ ያህል ጎላ ጎላ ያሉትን እንመልከት

ዋና ዋናዎቹ ጥያቄዎች የምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀምን፣ የፕሬስ ነጻነትን የሚመለከቱ ነበሩ፡፡ የምርጫ አስፈፃሚዎችን በተመለከተ ፓርቲዎቹ ያቀረቡት ጥያቄ "የገዥው ፓርቲ አባልና ደጋፊ በመሆናቸው በምርጫ ሂደት ላይ ወገንተኝነት ታይቷል" የሚል ነበር፡፡ ምርጫ ቦርድ ለዚህ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ፣ "ሰላሳ ሶስቱ ፓርቲዎች ይህን ቅሬታ ሲያቀርቡ የተባለው ችግር በየትኛው ክልል በተካሄደ ምርጫ የትኛው ምርጫ አስፈፃሚ ግለሰብ ወገንተኝነት እንደታየበት፣ ምን አይነት የወገንተኝነት ድርጊት እንደተፈፀመ በማስረጃ ተደግፎ አልቀረበም" የሚል ነበር፡፡

እርግጥ ነው በምርጫ ላይ ምንም አይነት ችግር አይፈጠርም ብሎ መደምደም አይቻልም፡ በመቶ ዓመታት የሚቆጠር የምርጫ ታሪክ ባላቸውም አገራትም ችግር ሊያጋጥም የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ እውነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ምርጫው የሚያክል የህዝብ የስልጣን ምንጭነትና ባለቤትነት የሚረጋገጥበት ትልቅ ጉዳይ ላይ እንደ ችግር የሚነሱ ጉዳዮች ተገቢውን መፍትሄ ማግኘት ይችሉ ዘንድ የተሟላ በማስረጃ የተደገፉ ተጨባጭ መሆን ይገባቸዋ ፡፡

በቂ ማስረጃ ሳይቀርብ የሚነሳ ቅሬታ በዘፈቀደ ከተነገረ አሉባልታ የተለየ ዋጋ አይኖረውም፡ በመሆኑም አንድነት/ መድረክ መሯቹ 28 ፓርቲዎች በዚህ ጉዳይ ላቀረቡት ጥያቄ የሚስተካከያ እርምጃ መወሰድ አይቻልም፡፡ ቦርዳም ይህንኑ ነበር ያስታወቀው፡፡ አንድነት/ መድረክ መሯቹ ፓርቲዎች "የተቃዋሚ ፓርቲ እጩዎች የወከሏቸው ታዛቢዎች በምርጫ ወቅት ታስረዋል፣ ተባረዋል" የሚል ቅሬታም አቅርበዋል፡፡

ይህ ቅሬታ ከዚህ ቀደም በተካሄዱት የ1997 እና የ2002 ምርጫዎችም ላይ መቅረቡን ብዙዎች ያስታወሳሉ፡፡ ምርጫ ቦርድም ለቅሬታው ምላሽ ሲሰጥ "በ2002 ምርጫ ወቅት የተወሰኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህን ቅሬታ አቅርበው ነበር፡፡" በማለት አስታውሷል፡፡ ቦርዱ በዚህ ዙሪያ ላቀረበው ቅሬታ በሰጠው ምላሽ ቅሬታው በቀረበበት የ2002 ምርጫ ወቅት፣ አቤቱታ በቀረበባቸው አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ ማጣራቱንና የተባለው ችግር ያለሜጠሩን አረጋግጦ አግባብ አለመሆኑን ማሳወቁንም አስታውሷል፡፡

እንግዲህ ከ2002 ወዲህ ሌላ ምርጫ ስላልተካሄደ ፓርቲዎቹ ማጣራት ተደርጎበት አለሚጣሙ የተረጋገጠን ጉዳይ ነው በድጋሚ እንደ አዲስ ያቀረቡት፡፡ ይህ ደግሞ ምርጫው ላይ ላለማተፍ ሰበብ ለሜለግ የተደረገ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከዚሁ ከታዛቢዎች ጋር በተያያዘ ሕዝብ የሚጣቸው ታዛቢዎች ለተለያዩ ተጽእኖዎች መደረጋቸውን ፓርቲዎቹ እንደ ቅሬታ አቅርበዋል፡፡ ምርጫ ቦርድ ለዚህ ቅሬታ በሰጠው ምላሽ፣ ከዚህ ቀደም ለሜጨሻ ጊዜ በተካሄደው የ2002 አገራዊ ምርጫ ላይ ሕዝብ የሚጣቸው የምርጫ ታዛቢዎች ላይ የዚህ አይነት ችግር ስለመኖሩ ከፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆነ ከሕብረተሰቡ የቀረበ ቅሬታ አለመኖሩን አስታውሷል፡፡

በወቅቱ አቤቱታ ያልቀረበበት ይህ ችግር አሁን በሜጪው ምርጫ ላይ ለማተፍ እንደችግር ሲቀርብ፣ ችግሩ የት እንደተፈፀመና ድርጊቱ የተፈፀመባቸው ሰዎች እነማን እንደሆኑ አለመቅረቡንም ቦርዱ አስታውቋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የተወሰኑ ተቃዋሚዎች አሁን "ተፅእኖዎች ተፈፅመውባቸዋል" በሜል ቅሬታ ያቀረቡባቸው የ2002 ምርጫ የሕዝብ ታዛቢዎችን ሕዝቡ በሚጠበት ወቅት "አሜራረጣቸው ትክክል አይደለም፣ ገለልተኛም አይደሉም" የሜል ቅሬታ አቅርበውባቸው እንደ ነበር ይታወሳል፡፡ ያኔ ገለልተኛ አይደሉም ሲባሉ የነበሩት የህዝብ ታዛቢዎች፣ አሁን ነገሩ ካለፈ በኋላ እንደተዘነጋ በማስብ "ተፅእኖዎች ተፈፅመውባቸዋል" ማለሱ የሚያስተዛዝብ ነው፡፡

ተቃዋሚዎቹ መገናኛ ብዙሃንን የሚሜለከቱ ቅሬታዎችም አቅርበዋል፡፡ በዚህ ቅሬታ ላይ የተለያዩ ጉዳዮችን አንስተዋል፡፡ ቀዳሚው "ፍትሃዊ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም የለም" የሜል ሲሆን ሁለተኛው "የግል ፕሬሶችና የፓርቲ ልሳኖች ተዘግተዋል፣ እንዳይታተሙ ተገደበዋል" የሜል ነው፡፡

የመገናኛ ብዙሃንን ፍትሃዊ አጠቃቀም፣ በተለይ ከምርጫ ጋር በተያያዘ ለቀረበው ቅሬታ ብሄራዊ ምርጫ ቦረድ በሰጠው ምላሽ፣ የምርጫ አዋጅ 523/99 አንቀጽ 59ን ጠቅሷል፡፡ በዚህ አዋጅ መሰረት "የፖለቲካ ድርጅቶች የመገናኛ ብዙሃን የአየር ሰዓት እንዴት ይጠቀሙ" የሚለው በግልፅ መቀመጡንና በዚሁ መሰረት የአጠቃቀም ደንብ መውጣቱንም አስታውቋል ፡፡ ደንቡ ፍትሃዊ መሆኑን ለሚረጋገጥ የፖለቲካ ፓርቲዎች በረቂቁ ላይ አስተያየት እንዲሰጠበት መደረጉንና፣ በዚሁ መሰረት የአየር ሰዓት ድልድል መደረጉን፣ በድልድሉም ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መወያየታቸውንም አስታውሷል፡፡

በ2002 ዓ/ም እና ከዚያ ቀደም በተደረጉት ምርጫዎች ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ የግል ዕጩ ተወዳዳሪዎችም አቋማቸውንና ፖሊሲያቸውን በመንግስት ሬድዮና ቴሌቭዥን እንዲሁም ጋዜጦች ሲያስተዋውቁ እንደነበር ብዙዎቻችን እናውቃለን፡፡ በክልልና በአገር አቀፍ ደረጃ የሚወዳደሩት አብዛኞቹን ፓርቲዎች ያወቅናቸው፣ በዚህ ራሳቸውንና አቋማቸውን ለህዝብ እንዲያስተዋውቁ በተሰጣቸው የሬድዮና የቴሌቪዥን ስርጭት የአየር ሰኣት ነበር፡፡

ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እንደገለፀው፣ በምርጫ ሂደት ወቅት ወጥተው የነበሩ መግለጫዎችና ዘገባዎች እንዳመለከቱት በወቅቱ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ የተሰጣቸውን የአየር ሰዓት በሙሉ አልተጠቀሙም ነበር ፡፡ በተለይ የተሰጣቸው የጋዜጣ አምድ አጠቃቀምን በተመለከተ የተመደበላቸውን የጋዜጣ ስፍራ ጭራሽ ያልተጠቀሙ ፓረቲዎችም ነበሩ፡፡ ይህ የሆነ ው በውጭ ተፅእኖ ሳይሆን በራሳቸው በፓርቲዎቹ ድክመት ነበር፡፡

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ሰላሳ ሶስቱ ፓርቲዎች "ፍትሃዊ የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም አልነበረም" በሚል ያነሱት ቅሬታ መሰረተ ቢስ ነው፡፡ የግል ፕሬሶችንና የፓርቲ ልሳኖችን በተመለከተ ወደቀረበው ስንመለስ፣ ጉዳዩ ከምርጫ ጋር ያለተገናኘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ቢሆንም ምርጫና ፕሬስ የሚገናኙት በመሆናቸው ሁኔታው ምን እንደሚመስል እንመልከት፡፡

እርግጥ ነው ከስርጭት ውጭ የሆኑ ጋዜጦች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ጉዳይ በተለይ የአንድነት ፓርቲ ልሳን የሆነ ው ፍኖተ ነፃነት የተሰኘ ልሳንን እንዲሁም ነፃ ፕሬስ ነኝ የሚለውን ፍትህ ጋዜጣን የሚመለከት ነው፡፡ የአንድነት ልሳን የሆነ ው ፍኖተ ነፃነትም ሆነ የግል ጋዜጣ ነኝ ባዩ ፍትህ ለበርካታ ጊዜያት እየታተሙ ሲሰራጩ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው ሃሳብን የመግለጽ ነፃነት በአፌዴሪ ሕገመንግስት ተረጋግጦ፣ ለዚሁ ነፃነት ተግባራዊነት የፕሬስ አዋጅ በመውጣቱ ነው፡፡

ሀሳብን የመግለፅ – የፕሬስ ነፃነት በሕገ መንግስት የተረጋገጠ ቢሆንም የህዝብን መብትና ነጻነት፣ ሰላም፣ … ለማጠበቅ ዓላማ የህግ ገደብ ተበጅቶለታል፡፡ የፕሬስ ነፃነት፣ በፕሬስ አማካኝነት በአገር ደሕንነት፣ በሕዝብና በግለሰቦች ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ድርጊት ሚፈፀምን አያጠቃልልም፡፡

በዚሁ መሰረት የተጠቀሰውን ጋዜጣና የፓርቲ ልሳን እንዳይታተሙ ያደረጋቸው በ1997 ዓ/ም ተሻሽሎ የወጣው የወንጀል ሕግ ነው፡፡ በወንጀል ሕጉ ምዕራፍ አራት ላይ "በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በሚደረጉ ወንጀሎች ተካፋይ መሆን" በሚለው ርዕስ በአንቀፅ 43 ስር በህትመት ውጤቶች አማካኝነት ወንጀሎች ተፈፅመው ሲገኙ የሚያስከትለውን ተጠያቂነት በተመለከተ ተደንግጓል፡፡

በዚህ አንቀጽ ላይ የሕትመት ውጤቶች ወንጀል ተፈጽሞ ሲገኝ ከሕትመት ውጤቶች አዘጋጆችና ከአሳታሚ ድርጅቶች ቀጥሎ በተዋረድ አታሚዎች(ማተሚያ ቤቶች)፣ አታሚዎቹ ባልታወቁበት ሁኔታ ደግሞ የህትመት ውጤቱ አከፋፋዮች እንደሚጠየቁ ይገልፃል፡፡

በዚህ መሰረት ማተሚያ ቤቶች አትመው በሚያወጡት የህትመት ውጤት ሳቢያ ከሚደርስባቸው የህግ ተጠያቂነት ራሳቸውን የሚከላከል መብት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለዚህም በአገሪቱ የሚገኙ የተወሰኑ አታሚዎች (ማተሚያ ቤቶች)፣ አሳታሚዎች በወንጀል የሚያስጠይቅ ይዘት ያለው የህትመት ውጤት ለሕትመት እንዳያመጡ፣ የሚያመጡዋቸው የህትመት ውጤቶች በሕግ ያስጠይቃሉ ብለው ሲያምኑ ለማተም እንዳይገደዱ ውል እንደገቡ ጠይቀው ከአታሚዎች ጋር የስራውል ገብተዋል፡፡ በዚህ ውል መሰረት በሕግ የሚያስጠይቅ ይዘት ያለው የህትመት ውጤት ይዘው የመጡ ጋዜጦችንና የፓርቲ ልሳኖችን እንደማያትሙ አሳወቁ፡፡ አንድነት/መድረክ መራሾቹ ፓርቲዎች በዚህ ዙሪያ ያቀረቡት ቅሬታ ከዚህ የህግ አግባብ አኳያ የሚታይ ነው፡፡

በዚህ አኳኋን ለጥያቄዎቹ ምላሽ ከተሰጠ በኋላ ፓርቲዎቹ ወደ ምርጫ ይገባሉ ተብሎ ሲጠበቅ አምስቱ ብቻ ማለትም፤ የኢትዮጵያ የፍትህና የዴሞክራሲ ኃየሎች ግንባር፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ኃይሎች ሕብረት፣ የሲዳማ አርነት ንቅናቄ፣ የባሕር ወርቅ ምስማስ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅትና ዱቤና ደጀን ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ቀርበው የምርጫ ምልክታቸውን ሲወስዱ የተቀሩት በአሻፈረኝ ባይነታቸው ፀኑ፡፡

የተቀሩት 28ቱ አንድነት/መድረክ መራሾቹ ፓርቲዎች ሰሞኑን ባወጡት መግለጫ የተደበላለቀ ነገር ነግረውናል፡፡ የፓርቲዎቹ አስተባባሪ ኮሚቴ ለአገር ወስጥ ጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ "ከፓርቲዎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማጠናከር፣ ምርጫው ፍትሃዊ፣ ተዓሚኒና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለማካሄድ የሚያስችሉ ግልፅና የሚያሻማ ቢሆኑም ቦርዱ 'ጆሮ ዳባ ልበስ' በማለት ለጥያቄዎች መፍትሄ ሳይሰጥ ወደምርጫ አፈፃፀም ገብቷል" ብለዋል፡፡

እርግጥ ነው ቀደም ሲል የተማለከትናቸው ፓርቲዎቹ እንደ ችግር ያነሱዋቸው ጉዳዮች ምርጫው ፍትሃዊ፣ ተዓሚኒና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ያግዛሉ፡፡ምርጫ ቦርድም ይህን ታሳቢ በማድረግ አንድም ጥያቄ ሳያስቀር ምላሽ ሰጥቷል፡፡ምላሽ ከተሰጠባቸው ቅሬታዎች መሃከል የተወሰኑት ጉዳዮች በቀጥታ ከምርጫው ጋር የሚገናኙ ሰላም፤ ዴሞክራሲንና ሰብአዊ መብቶችን ለማስከበር የተወሰዱ ሕጋዊ እርምጃዎችን የሚማለከቱ ሲሆኑ፣ የተቀሩት ደግሞ ከዚህ ቀደም ተነስተው ምላሽ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከምርጫ ጋር ተያይዞ በቀጣየነት ችግሮቹ ቢያጋጥሙ መፍትሄ መስጠት የሚያስችል ሕግና የአሰራር ስርአት ተዘርግቷል፡፡

ችግሮቹን ለመከላከል ከተዘረጉት የአሰራር ስርአቶችና ሕጎች መሃከል ከ2002 ምርጫ ቀደም ብሎ ከአንድነት/መድረክ በስተቀር የተቀሩት ሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለወራት መክረውበት ያፀደቁት፣ በኋላም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሆኖ የወጣው የምርጫ ስነ ምግባር ደንብና በዚሁ ደንብ መሰረት የተቋቋመው የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ዋነኛው ነው፡፡ ይህ ስርአት ከምርጫ ጋር የተያያዙ ችግሮች ላይ ፓርቲዎች አስቀድመው እንዲወያዩ፣ ከተፈጠሩም በኋላ መፍትሄ እንዲያገኙ ማድረግ ያስችላል፡፡

አሁን ችግሮቹ ገና ለገና በሚጨው የአዲስ አበባ፣ የድሬደዋና የአካባቢ ምክር ቤቶች ምርጫ ላይ ያጋጥማሉ በሚል ምናባዊ ስሌት 27 ፓርቲዎችን አሰባሰቦ የወዝግብ አጀንዳ ለመፍጠር የሚፍጨረጨረው አንድነት/መድረክ፣ ከምርጫ ጋር ተያይዘው ሊያጋጥሙ ለሚችሉ ችግሮች መፍትሄ ለማበጀት የተዘጋጀውን ሕግና የአሰራር ስርአት አሻፈረኝ ማለቱ ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ አንድነት/መድረክ በሚጨው ምርጫ ላይ የያዘው አቋም ዋና ትኩረቱ ምርጫ ላይ ተሳትፎ የህዝብ ወክልና ማግኘት ሳይሆን፣ ምርጫን ለስወር አላማ ማስኪያነት ለማጠቀም የወዝግብና ጭቅጭቅ መንስኤ እንዲሆን ማድረግ መሆኑን ያመለክታል ፡፡

እንግዲህ አንድነት/መድረክ መራሹ የፓርቲዎች ቡድን ሰብሳቢ የሆኑት የአንድነቱ ከፍተኛ አመራር አቶ አስራት ጣሴ ከአሜሪካ ድምፅ የአማርኛ ፕሮግራም ጋር ባደረጉት ቃለመጠይቅ ወደ ምርጫው እንደሚገቡ አሳወቀዋል፡፡ እርግጥ አቶ አስራት ይህን ከማለታቸውም በፊት ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫው ላይ መወዳደር የሚፈልጉ ፓርቲዎች የምርጫ ምልክታቸውን እንዲያሳወቁ በስቀመጠው ከአንድ ወር በላይ የግዜ ገደብ ወስጥ ቀርበው የምርጫ ምልክታቸውን ባለማሳወቃቸው በራሳቸው ወሳኔ ከምርጫው ወጪ ሆነዋል፡፡ ቦርዱም ይህን አሳወቋል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጉዳይ ፓርቲዎቹ ከምርጫ ወጭ መሆናቸው ሳይሆን ከምርጫ ወጭ እንዲሆኑ ያደረጋቸው ምክንያት ምንድ ነው? የሚለው ነው፡፡

ይህ ከምርጫ ወጭ የመሆን ፍላጎት አንድነት/መድረክ ያሰባሰባቸው የሁሉም ፓርቲዎች ከወስጥ የመነጨ ፍላጎት ነው ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ምርጫው ላይ ያለመሳተፍ ጉዳይ በዋናነት የአንድነት/ የመድረክ አጀንዳ ነው ፡፡ ለዚህ አስረጂ መጥቀስ ይቻላል፡፡ የመድረክ አባል መሆኑን የሚፎገረው፣ ሆኖም ከመድረክ ወጭ አቋም በማያዝና ጮሆ በመናገር የሚታወቀው የአንድነት አመራሮች በቅርቡ ይፋ ያደረጓቸውን አቋሞች በአስረጅነት እንመልከት፡፡ እነዚህ የአንድነት አመራሮች ሊቀመንበሩ ዶ/ር ነጋሦና የፖለቲካ ጉዳይ ሃላፊ የሆኑት አቶ መላቱ ጣሴ ናቸው፡፡ ሁለቱ የአንድነት አመራሮች በሕዳር ወር ላይ እንዳቀረቡት በተነገረላቸው ጥናት የገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ችግሮች ያሉዋቸውን ዘርዝረው፣ ገዥው ፓርቲ "የሕዝብ ድጋፍ የለውም" የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል፡፡

ሁለቱ የአንድነት አመራሮች "ገዢው ፓርቲ የሕዝብ ድጋፍ የለውም" በሚል ያቀረቡትን ድምዳሜ የተመለከተ ማንኛወም ሰው አንድ የሚያምተውና የሚጠበቀው ነገር አለ፡፡ ይህም ፓርቲው በምርጫ ላይ ተሳትፎ በኢህአደግ ላይ አኩርፈዋል ያላቸውን ዜጎች ድምፅ ለማግኘት ይሰራል የሚል ነው፡፡ የአንድነት አመራሮች ግን ከዚህ የተለየ አቋም መያዛቸምን ነው የገለፁት፡፡

ዶ/ር ነጋሦ ኢህአዴግን ሕዝቡ እንደሚደግፈው በእርግጠኝነት ተናግረው ሲያበቁ፣ ምርጫ ላይ ተሳትፈን በሕዝብ ወክልና ወደ ስልጣን እንመጣለን ከማለት ይልቅ "ገዢውን ፓርቲ ለለወጥ የሚያስገድደው ሰፊ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ገዢውን ፓርቲ ለማስወገድ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ የሚፈጠርበትን መንገዶች መቀየስና በእርሱ ላይ መስራት የወደፊት የትግል አቅጣጫችን ነው" ነበር ያሉት፡፡ በተመሳሳይ የፓርቲው የፖለቲካ ጉዳዮች ኃላፊ አቶ መላቱ ጣሰው "ሕዝቡ ለወጥን ከተቃዋሚዎች ማጠበቅ አይኖርበትም፤

ሕዝቡ በራሱ ትግል ነፃ መውጣት አለበት፣ ፓርቲዎች የሕብረተሰቡን ትግል ይመራሉ ” ብለው የሕዝባዊ እንቅስቃሴ አስፈላጊነትንና የፓርቲያቸውን ሚና ነግረውናል፡፡

ዘንድሮ ሚያዚያ ወር ላይ የሚካሄደው የአዲስ አበባ ምክር ቤትና የአካባቢ ምርጫ በሂደት ላይ እያለ፣ የአንድነት ፓርቲ አመራሮች በይፋ የገለፁዋቸው እነዚህ አቋሞች፣ ፓርቲው ምርጫ ላይ የመሳተፍ ፍላጎት እንደሌለው፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ወሳኔ ላይ መድረሱንም ያሳያል፡፡ እናም አንድነት/መድረክ መራሹ ቡድን ምርጫው ላይ ላለመሳተፍ የሚያቀርቡዋቸው ጉዳዮች፣ ሕዝብንና ሌሎች ታዛቢዎችን ሊያታልል የሚችል ሰበብ ለማቅረብ የተደረገ ነው፡፡ እዚህ ላይ አንድነት/መድረክ ይህን በምርጫ ከሚገኝ የሕዝብ የስልጣን ውክልና ውጭ በሕዝባዊ እንቅስቃሴ በሌላ አነጋገር በኃይል ለስልጣን ሊያበቃ ይችላል ያለውን አካሄድ ለምን መረጠ? የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ በተለይ ሕዝቡ ገዢውን ፓርቲ እንደሚደግፍ እርግጠኛ ነኝ እያለ ምርጫን መሸሹ ብዙዎችን ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡

ለዚህ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ቀዳሚው ግን በተለይ አንድነት ያያዛቸው ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲዎች ያረጁና ያፈጁ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት ሊኖራቸው የማይችሉ በመሆኑም በምንም አኳኋን ለስልጣን የሚያበቃ የሕዝብ ድምፅ ሊያስገኙ የማይችሉ ከመሆናቸው የነሚጨ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የተለያየ ማንነት ያላቸው ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች አገር ነች፡፡ እነዚህ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ማንነታቸው እወቅና ተነፍጎት፣ በማንነታቸው አንገታቸውን እንዲደፉ የሚያደርግ በረጅም ዘመን ጭቆና ወስጥ አልፈዋል፡፡ ኢትዮጵያ የምትባለዋ አገር ከተመሰረተች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህ የጭቆና ቀንበር ከላያቸው ላይ የወረደው በ1983 ዓ/ም የመጨረሻው ጨቋኝ የሆነው የወታደራዊው ቡድን አምባገነናዊ ስርዓት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ባካሄዱት መራራ ትግል ተገርስሶ መወደቁን ተከትሎ ነው፡፡

ይህን ተከትሎ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የሉአላዊት ኢትዮጵያ ባለቤቶች ሆነው በእኩልነትና በመከባበር ላይ ተመስረተው ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ መኖር የሚያስችላቸውን የቃል ኪዳን ሰነድ – የኢፌዴሪ ሕገመንግስት ቀርፀዋል፡፡ በዚህ የቃል ኪዳን ሰነድ መሰረት ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ከሌሎች ጋር በእኩልነት መኖር የሚያስችል ፌደራላዊ ስርዓት መስርተዋል፡፡ ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እስከመገንጠል የዘለቀ መብትና ነፃነትም አላቸው፡፡

አሁን ኢትዮጵያ ወስጥ ከሚንቀሳቀሱት አይነ ግብ ነን ከሚሉት ፓርቲዎች መሃከል ይህን የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በሕገ መንግስቱ የተጎናፀፉትን የብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት መከበሩ ዋነኛ ሚረጋገጫ የሆነውን ራስን በራስ የማስተዳደር መብት በመቃወም ቀዳሚው አንድነት ነው፡፡

በመድረክ ወስጥ ከብሔራዊ ፓርቲዎች ጋር ጥምረት መመስረቱን ከተናገረ በኋላ እንኳን በዚህ አቋሙ ላይ ለወጥ አላሳየም፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ወስጥ ወሳኝ በሆነው በዚህ ጉዳይ ላይ ያለውን አቋም ሳይቀይር

በመድረክ ስር ከብሄራዊ ፓርቲዎች ጋር ተጣምሬያለሁ ማለቱ ብዙዎችን የሚያስገርም እንቆቅልሽ የሆነውም ለዚህ ነው፡፡ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ጥምረቱ የሌለ ያህል ከሌሎቹ ተጣማጆቹ ተለይቶ ለብቻው አቋም እንዲይዝ የሚያስገድደው ከሌሎቹ ጋር ሊዋሃድ የሚችል ወሃና ዘይት መሆኑ ነው የሚሉ አስያየት የሚሰጡም አሉ፡፡

ያም ሆነ ይህ አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አወቃቀር በአፌደሪ ሕገመንግስት ላይ ከተደነገገው በተቃራኒ በብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች አሰፋፈር ሳይሆን፣ በሚሊክአ ምድር – በወንዝ፣ ተራራ ሸለቆ መከለል አለበት የሚል ፅኑ አቋም ነው ያለው፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችን በማብታተንና የተለያዩትን በመቀላቀል በአፌዴሪ ሕገመንግስት የተጎናፀፉትን ራስን በራስ እያስተዳደሩ በእኩልነትና በመከባበር አንድ የጋራ አገር መስርተው የመኖራቸውን ጉዳይ የሚያቻል ያደርዋል፡፡

በመሆኑም አንድነት በተለያዩ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች የሚገለፁትን ኢትዮጵያውያን ድጋፍና ለስልጣን የሚያበቃ ድምፅ ማግኘት እንደማይችል ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ስለዚህ ስልጣን ላይ ወጥቶ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች በመራራ ትግል አሸቀንጥረው የጣሉትን ስርዓት ዳግም የመመለስ አቋሙን ተግባራዊ ለማድረግ ከምርጫ የተለየ አካሄድ መከተል አለበት፡፡ ይህም አነሰም በዛም በተለይ በከተሞች አካባቢ የሚገኙ ከባለፉት ዘውዳዊና ወታደራዊ ስርአቶች አማካከት ወርደኝት ያልጸዱ ደጋፊዎቹን አስተባብሮ በኃይል የመንግስት ስልጣን ለማያዝ መንቀሳቀስ ነው፡፡

በውጭ አገራት በተለይ ሰሜን አሜሪካና አወሮፓ የሚኖሩ – ገሚሶቹ የዋህ የመኖሪያ ፍቃድ በማጠበቅ ላይ የሚገኙ፣ ገሚሶቹ የባለፉት ስርዓቶች ታሪክ ሆኖ መቅረት የከነከናቸው፣ የተቀሩት ደግሞ በተለይ በአፋኙ የደርግ ስርአት በፈፀሙት ወንጀል በሕግ ስለሚፈለጉና እንፈለጋለን ብለው ስለሚጠረጠሩ ወደ አገር ቤት መመለስ የማይችሉ ኢትዮጵያውያንና ትወልደ ኢትዮጵያውያን ከጀርባ ሆነው የሞራልና የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ አንድነት በአቋሙ እንዲፀና ምክንያት መሆናቸውንም የሚያመለክቱ ሁኔታዎች አሉ፡፡ የአንድነት/መድረክ አመራሮች ከሁለት ወራት በፊት በሚጨው ምርጫ ላይ እንደሚሳተፉ የሚያመለክት አዝማሚያ ከማሳየታቸው በፊት ወደ አሜሪካ ተጉዘው እንደነበር ይታወሳል፡፡

አሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትወልደ ኢትዮጵያዊያን በምርጫው ላይ ድምፅ እንደማይሰጡ ይታወቃል፡፡ ታዲያ የአንድነት/መድረክ አመራሮች ወደ አሜሪካ የተጓዙት ለስልጣን የሚያበቃ መራጭ ፍለጋ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ተልዕኮ አስታጥቆ ማስፈፀሚያ ገንዘብ የሚሾጉጥላቸው ፍለጋ ነው፡፡ በዚህ ጉዳው ላይ በተለያዩ አጋጣሚዎች እዛው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትወልደ ኢትዮጰያዊያን ምክርነታቸውን ሰጥተውበታል፡፡

ከዚህ ቀደም ካለን ልምድ በውጭ አገር የሚኖሩ በማስረተ በስ ጥላቻ የሚነዱ ስሜታዊ ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊያንና ትወልደ ኢትዮጰያዊያን "ምን እናድርግ?" ብሎ ለሚጄድላቸው ፓረቲ "ምርጫ ላይ ተሳተፍ"

የሚል አደራ እንደሚዩሰጡ ይታወቃል፡፡ እናም አንድነት በቅርቡ የተቀበለ ተልዕኮ ሊሆን የሚችለው፣ ከጠቅላላ የአገሪቱ ሕዝብ አብላጫ ባይሆንም፣ ምርጫ አስታካችሁ ደጋፊያችሁን በማስተባበር "በሕዝባዊ እንቅስቃሴ" የማግስት ለወጥ አምጡ የሚል ነው፡፡የአንድነት አመራሮች ከአሜሪካ ሚሊስ ባካሄዱት ስብሰባ ይህንኑ ነው በይፋ ተናግረዋል፡፡

ፅንፈኛ ተቃዋሚዎን ዳያስፖራ በተማለከተ የመድረክ ከፍተኛ አመራር የሆኑት ፐ/ር በየነ ጴጥሮስ ከአንድ ወር በፊት ሰንደቅ ከተባለው ሳምንታዊ የአማርኛ ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ የነገሩንንም ለዚህ አስረጂነት መጥቀስ ይቻላል፡፡ ፐ/ር በየነ "ዲያስፖራው አንድ ስብሰባ ላይ መጥቶ 50 ዶላር ከፍሎ በዛች 50 ዶላር መንግስት ለምን አትገለብጡም ይላል። ያለው ኢህአዴግ ደግሞ የሚዩፈለጥ አለት ነው።" ነበር ያሉት፡፡

ያም ሆነ ይህ አንድነት/መድረክ ይህን ዓላማውን ማስካት እንደሚዩችል ያወቀዋል፡፡ስለዚህ አጋር ይፈልጋል፡፡ በቅርብ ያገኛቸው አጋሮቹ ከምርጫ ጋር አያይዞ በቅቤ ምላሱ ያልሆነ ነገር ቀባጥሮ ሊሸወዳቸው የሚችላቸውን ተቃዋሚ ፓረቲዎች ነው፡፡ በዚህ አካሄድ "በምርጫው ላይ ተሳትፋችሁ ላታሸንፉ ኢሕአዴግን ከምታሩዋሩጡ፥ ከምርጫ ውጭ ሆናችሁ እኔን አሩዋሩጡ" ብሎ ጀንጅኖ እስካሁን ባለው ሁኔታ 27 ያህል ፓርቲዎችን ለአሯሯጭነት አዘጋጅቷል፡፡

እነዚህ አንድነት/መድረክ አደናግሮ የማለማቸው አሯሯጮቹ ከሩጫው አንዳችም ጥቅም አያገኙም፡፡ እርግጥ አንድነት/መድረክ ዶላር ሊያገኝ ይችላል፡፡ ፓርቲዎቹ የተጠቋቋማለትን አላማ የማስካት እድል ያገኙ የነበረው በምርጫው ላይ ቢሳተፉ ነበር፡፡ ቢያንስ ከሕዝብ ጋር የመተዋወቅ እድል ያገኙ ነበር፡፡ ለአንድነት/መድረክ ብለው ይህን እድል ማስዋዕት አድርገዋል፡፡

አሁንም ቢሆን ግን አልረፈደባቸውም፡፡ በአንድነት/መድረክ ስር ሆነው ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ለማስራት መሚልማላቸውን ተገንዝበው፣ ከዚህ በሚራቅ ቢያንስ በቀጣዩ ምርጫ ላይ ለማሳተፍ ማስራት የሚቻሉበት እድል አሁንም ክፍት ነው፡፡